# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች

# ኢየሱስ እና አላዛር።




ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org



©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ማርያምና ማርታ ተጨንቀዋል። ወንድማቸው አላዛር እጅግ ታምባቸዋል። እህቶቹ አላዛር በቅርብ ሊሞት እንደሚችል ያውቁ ነበረ። ኢየሱስንም አስጠሩ። እየሱስ ይሔንን ትንሽ ቤተሰብ ከቢታንያ ጀምሮ ያውቅ ነበረ።



ኢየሱስ ስለ አላዛር ሲሰማ ፣ ለደቀመዛሙርቱ “ይሔ ህመም ለሞት አይሆንም” ይላቸው ነበረ፡፡ ምንም እንኳን ኢየሱስ በብዙ ርቀት አብሮአቸው ባይሆንም ፣ በአላዛር ሕይወት ምን ሊሆን እንደሚችል ያውቅ ነበረ፡፡



3

ቢታንያን ከመልቀቁ አስቀድሞ ኢየሱስ ሁለት ቀናትን ጠበቀ፡፡ ከዚያም ፣ ደቀመዛሙርቱን ያስጨነቃቸው አንድ ነገር ተናገረ፡፡ “አላዛር ሟቷል፤ እዛ ባለመሆኔ ደስተኛ ነኝ ምክንያቱም ይሔ እንድታምኑ ምክንያት ነው፡፡” እነዚህ አዲስ ቃላት ትርጉማቸው ምንድነው; ኢየሱስ ማድረግ የፈለገው ምንድነው?



4




5

ማርታ ኢየሱስን ልታገኘው ሔደች፡፡ ኢየሱስም እንዲህ አላት ፣ “ ወንድምሽ ከሞት ይነሳል፡፡” ማርታም እንዲህ ብላ መለሰችለት ፣ “በትንሳኤ ቀን ይሄ እንደሚሆን አውቃለሁ፡፡” እርሷ የመሰላት አላዛርን ዳግም የምታየው ፣ በመጨረሻው ቀን እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ያለው ከዚህ የተለየ ነው፡፡



6




7

አላዛር በመሞቱ ምክንያት ሁሉም እጅግ አዝኖ ነበረ፡፡ እህቱ ማርያም ታለቅስ ነበረ፡፡ ወዳጆቿም ያፅናኗት ነበረ፡፡ ኢየሱስም ያለቅስ ነበረ፡፡



8


ኢየሱስም ከሰዎችጋ ወደ መቃብር
ቦታው ሔደ፡፡ ትልቅ ድንጋይ
በመዝጊያው ላይ ተቀምጦ ነበረ፡፡
9


ኢየሱስም እንዲህ ብሎ አዘዘ ፤”ድንጋዩን
አንከባልሉት፡፡” ማርታም እንዲህ ብላ
መለሰች ፤ “አራት ቀን ስላለፈው ፤
በዚህን ሰዓት እጅግ ይሸታል፡፡”
10


በኢየሱስ ትዕዛዝ ሰዎቹ
ድንጋዩን አንከባልለው
አነሱት፡፡ ኢየሱስም ወደ ሰማይ
አባቱ ጸለየ፡፡ ኢየሱስም እዛ ያሉ
ሰዎች በእግዚአብሔር የተላከ
መሆኑን ያውቁ ዘንድ ተዓምራት
ሊያደርግ ተዘጋጀ፡፡
11


ኢየሱስም “አልአዛር”
ብሎ ጮኸ፡፡ “ውጣ”
አለው፡፡ ሰዎቹ ወደ ዋሻው
በመገረም ተሞልተው
እየተመለከቱ ሳይሆን
አይቀርም፡፡
12


አዎ!
አልዓዛር
ከዋሻው
ውስጥ ወጣ ፤
በልብስ
እንደተከፈነ
ከዋሻው ውስጥ
- ሕያው ሆኖ፡፡
13


ኢየሱስም አለ ፤ “ፍቱት”፡፡ እንዲሄድ ፍቀዱለት፡፡
እንዴት ያለ ደስታ ነው! እንባ ሁሉ ወደ ሳቅ
ተለወጠ፡፡ ኢየሱስ ቃሉን ጠበቆ ነበረ፡፡
አልዓዛር ሕያው ነው፡፡ የእግዚአብሔር
ልጅ ብቻ ነው ለሙታን ሕይወትን
የሚሰጠው፡፡
14

ይሄንን ተዓምር ያዩ ብዙዎች በኢየሱስ አመኑ፡፡ ነገር ግን አንዳንዱ የመቅደስ አዛዥ ለሆኑት ለጠላቶቹ ተናገረ፡፡ በቅንዓትም ተነሳስተው ኢየሱስን ለመግደል አሴሩ፡፡ ኢየሱስም ይሄንን ሲያውቅ ፣ ለተወሰነ ጊዜ ራሱን ሰወረ፡፡



15

ኢየሱስ እና አላዛር፡፡

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

ዮሐንስ 11

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት 119:130**

16




52 60

17

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16

18